የሰ/መ/ቁ.22094

22/06/98

ዳኞች፦ 1- አቶ መንበረፀሀይ ታደሰ

2- አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

3- አቶ ጌታቸው ምህረቱ

4- አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5- ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፦ የኢት/ብረታ ብረት ማቅለጫ ፋብሪካ

ተጠሪ፦ አቶ በቀለ ነጋሽ

በዛሬው እለት ግራ ቀኙ ቀርበው ችሎቱ ክሱን ከሠማ በኋላ ተከታዩን ውሣኔ ሠጥቷል።

## ው ሣ ኔ

በግራ ቀኙ መሀከል ለነበረው ክርክር መነሻ የሆነው ተጠሪ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የምሠራበት የምስማር ምርት ማጠቢያ ማሺን ኦፕሬተርነት የሥራ መደብ ስለሚገባኝ የሥራ መደቡ ከደሞዙ ጋር እንዲሠጠኝ ሲሉ ያቀረቡት ክስ ነው። በመሆኑም ይህ ችሎት ቦርዱ የተጠሪን ክስ ተቀብሎ ለማስተናገድ ሥልጣን አለው ወይ? የሚለውን ነጥብ ተመልክቷል።

የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በአዋጁ ለማየት ሥልጣን የተሠጠው የወል የስራ ክርክር ጉዳዮችን ነው። የወል የሥራ ክርክር ማለት ደግሞ የክርክሩ ውጤት በአንድ ሠራተኛ ላይ ተወስኖ የሚቀር ሣይሆን አጠቃላይ የሠራተኞች የጋራ መብትና ጥቅምን የሚነካ ማለት መሆኑ በመ/ቁ 18180 ትርጉም ተሠጥቶታል። ከዚህ አንፃር የተጠሪን ጥያቄ ስንመለከት የተጠሪውን የግል ጥቅምና መብት ለማስከበር የቀረበ እንጂ ከተጠሪው አልፎ የሌሎች ሠራተኞችን የጋራ መብትና ጥቅም የሚነካ አይደለም። በመሆኑም ክርክሩ የግል የሥራ ክርክር ነው። የግል የሥራ ክርክርን ደግሞ ቦርዱ ለማየት ሥልጣን የለውም። በዚህም ምክንያት የተጠሪን ጥያቄ ቦርዱ ያለ ሥልጣኑ ተቀብሎ ማስተናገዱና ቦርዱ

7/7/98

በሠጠው ውሣኔ ላይ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀብሎ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ/ቁ 166/02/97 በ18/9/97 እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ.ቁጥር 39605 በ6/03/98 የሰጡት ውሣኔዎች ተሽረዋል:: ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ:: መዝገቡ ተዘግቷል::

7/3/98

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ወ.ፈ